# “አጽናኑ ሕዝቤን አጽናኑ”

ኢሳይያስ 40:1

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው ሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ ላለፉት ሃያ አንድ ዓመታት ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ለማስከበርና በስደትና በመገፋት ውስጥ ያለውን ሕዝበ ክርስቲያን በማጽናናትና በአንድነት በማሰባሰብ ቤተ ክርስቲያንን ሲመራ መቆየቱ ለሁሉም ግልጽ ነው።

በተለይም ሕገ ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ ላለፉት ሃያ አንድ ዓመታት ተደብቀው የነበሩ እውነታዎች ዛሬ በአደባባይ ግልጽ ሆነዋል። ሆኖም ይህን የቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ጥሰት ዋጋ ባለመስጠትና የራስን ጥቅም በማስቀደም ከአርባ ሚሊዮን በላይ የሆነውን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታይ ድምጽ በማፈን በአዲስ አበባ የሚገኙ በጥቅምና በስልጣን መንፈስ የታወሩ ጥቂት አባቶች በሥልጣን ላይ ባሉ የፖለቲካ ኃይላት ተደግፈው በፓትርያርክ ላይ ሌላ ፓትርያርክ ለመሾምና የቤተ ክርስቲያንን የመከራ ዘመን ለማራዘም በአሁን ወቅት በመውደቅና በመነሳት ላይ እንዳሉ ይታወቃል።

በመሆኑም ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በሎስ አንጀለስ ከተማ ባካሄደው አስቸኳይ ልዩ ጉባኤ ቤተ ክርስቲያን ያጋጠማትን አሳዛኝ ሁኔታ በመገምገም፥ በሐዘን ላይ ያለውን ሕዝባችንን የሚያጽናና ለሥራ የሚያነሣሣ ታላቅ ዓለም አቀፍ የስብከተ ወንጌል ጉባኤ በመላው ዓለም በሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ ሥር በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትና በተለያየ ምክንያት በልዩነት በቆዩት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ በአስቸኳይ እንዲደረግ በተወሰነው መሠረት ታላቅ መንፈሳዊ የስብከተ ወንጌል ፕሮግራም ተዘጋጅቶል።

በተለይም የዚህ ዓለም አቀፋዊ የስብከተ ወንጌል ጉባዔ ዋና አላማ፤

፩. በስደት ላይ ያለው ሕዝበ ክርስቲያን በአንድነት በመጽናትና በመቆም እስከአሁን ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ለማስከበር የከፈለውን መስዋእትነት ዋጋ በመስጠት የበለጠ እንዲበረታና በእምነቱ እንዲጸናና ለእውነት እንዲመሰክር ማድረግ፤

፪. ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በተደራጀ ሁኔታ እንዲቀጥል ለማስቻል በአዲስ መንገድ የሚቋቋመውን የመንበረ ፓትርያርክ ሕንጻ ሥራ በገንዘብ፥ በሐሳብና በጉልበት እንዲረዱ ለሕዝበ ክርስቲያን ጥሪ ማድረግ፤

፫. ቅዱስ ፓትርያርኩ በግፍ ከመንበረ ፓትርያርካቸው መነሣታቸውን መላው ዓለም እየመሰከረ ባለበት ወቅት በአዲስ አበባ የሚገኙት ጥቂት አባቶች በፖለቲካው ክንድ ተደግፈው የሚነዙትን የሐሰት ምስክርነት ማጋለጥ፡

፬. በውጭ ዓለም በስደት የምትገኘውን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አንድነትና ሰላም መጠበቅና ማስጠበቅ የሚሉት ተቀዳሚ አላማው ይሆናሉ።

ይህ ዓለም አቀፍ የስብከተ ወንጌል ጉባኤ ከየካቲት ፳፪ ቀን ፪ሺ ፭ ዓ.ም (March 1, 2013) ጀምሮ በዓለም ዙሪያ ባሉት አብያተ ክርስትያናት ዘንድ የሚሰጥ መሆኑን ለኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች በሙሉ በአክብሮት እንገልጻለን።

# ዓለም አቀፍ የስብከተ ወንጌል ፕሮግራም የሚደረግባቸው የአብያተ ክርስቲያናት ስም ዝርዝር እና ቀናት

ኒዮርክ ጽዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ... April 19-21, 2013
ባፍሎ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ... March 15-17 , 2013
ኒውጀርሲ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ... April 5-7, 2013
ኒውጀርሲ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ... April 12-14, 2013
ዲሲ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ... March 15-17 , 2013
ዲሲ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ... March 29-31, 2013
ሻርለት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ... March 15-17 , 2013
ኦሃዮ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ... March 29-31, 2013
አትላንታ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ... March 29-31, 2013
አትላንታ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ... April 5-7, 2013
ኮሎራዶ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ... April 19-21, 2013
ምኒሶታ ቅዱስ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን ... March 22-24, 2013
ፍሎሪዳ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን ... April 12-14, 2013
ላስቬጋስ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ... April 5-7, 2013
ሳንዲያጎ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ... April 5-7, 2013
ሎስ አንጀለስ ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ... March 29-31, 2013
ሎስ አንጀለስ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ... April 12-14, 2013
ኦክላንድ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ... March 29-31, 2013
ሳክራሜንቶ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ... April 5-7, 2013
ሳንሆዜ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ... March 15-17 , 2013
ሲያትል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ... March 22-24, 2013
ዳላስ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ... April 19-21, 2013
ኮሎራዶ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ... March 22-24, 2013
ዩታ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ... March 22-24, 2013
ሳውዝ ዳኮታ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ... April 12-14, 2013
ባልቲሞር ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ... April 26-28, 2013
ታምፓ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ... April 19-21, 2013
ሂዩስተን ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ... April 5-7, 2013

በካናዳ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ... March 1 to May 26, 2013
በአውሮፓ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ... March 1 to May 26, 2013
በአፍሪካ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ... March 1 to May 26, 2013
በአውስትራልያ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ... January 15 to May 26, 2013
በኒውዝላንድ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ... March 1 to May 26, 2013

"እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል፥ ስለዚህም እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር በምንጽናናበት መጽናናት በመከራ ሁሉ ያሉትን ማጽናናት እንችላለን።"
(፪ኛ ቆሮ. ፩:፬)